# “የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!”

## ያላበቃ መፈክር

ከ18 ወራት እስር በኋላ የቅንጅት መሪዎችና አባላት ከወያኔ እስር ቤት በመፈታታቸው የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች፤ በኢትዮጵያ አንድነት ለተሰለፋችሁ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች፤ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ። በግፍ ለታሰሩት የቅንጅት መሪዎች መፈታት በተለያየ መልኩ አስተዋጽዎ ያደረጋችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ፡ የሲቪክ ማህበራት፡ የሃይማኖት አባቶች፡ አዛውንቶች፡ ታዋቂ ግለሰቦች ሁሉ እልህ አስጨራሹ ልፋታችሁ በመጠኑ ውጤታማ፡ ስኬታማ በመሆኑ እሰየው ያሰኛል። የቅንጅት መሪዎች በመታሰራቸው ምክንያት በየአካባቢው፡ በየትምህርት ቤቱ ሳታቋርጡ ለመፈታታቸው አበክራችሁ ስትጮሁ ለእስር የተዳረጋችሁ፡ አሁንም የት እንደደረሳችሁ ቤተሰብ ያላወቃችሁ፡ በወያኔ በትር አካለ ስንኩል የሆናችሁ፡ የተደበደባችሁ፡ የተንገላታችሁ፡ የተሰደዳችሁ፡ ለወያኔ ጥይት ሰለባ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን በተለይ የሀገሪቷ አለኝታ ወጣቶች ተጋድሎአችሁን ታሪክ አይረሳውም። በቆራጥነትና በጽናት ታግላችኋል፡ ጮኃችኋል፡ መስዋትነት ከፍላችኋል። አሁንም የሕዝብ መብትና ሥልጣን እስኪረጋገጥ ትግሉና ትግላችን ይቀጥላል።

ግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ የወያኔ አምባገነንነትና ጨፍጫፊነት ይበልጥ በአደባባይ እርቃኑን የተጋለጠበት፡ ወያኔ ማን ነው? ምንድን ነው? ግራ ለሚላቸው መልስ የሰጠበት፡ አሸባሪ፡ አፋኝ፡ ጨፍጫፊ፡ ገዳይ መሆኑን ራሱ ለራሱ የመሰከረበት፡ “እኔን እንጂ...አትመልከት ሌላ” የዘፈነበት፡ በየደቂቃው ያላመቸውን ሕግ የሚሰርዝበት፡ በየሰከንዱ ያመቸውን ሕግ የሚያውጅበት፡ ተደፈርኩ ብሎ መርዙን የረጨበት፡ ለግድያ ያቅራራበት፡ የደም ጥማት አራራውን የተወጣበት ጥሩ አጋጣሚ ያገኘበት ቢኖር ያ ወቅት ነው።

ወያኔ ሕዝብ ድምጽ የሰጣቸውን የቅንጅትና የኅብረት አባላትን ያሳደደበት፡ የጨፈጨፈበት፡ ያሰረበት፡ የገደለበት፡ ከግለሰብ እስከ ፖለቲካ ድርጅት ከፊቴ ዞር በሉ ያለበት፡ ለወያኔ ካልበጀ ዲሞክራሲ የተወነጀለበት፡ የራሱን አፋኝ ሕገ መንግሥት እንዳሻው የጣሰበት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ምርጫ በወያኔ ማዕከልነት ለሚደረግ የሥልጣን የበላይነት መገዛት፡ ምርጫ የወያኔን ዲሞክራትነት ለማድመቅ መተባበር፡ ምርጫ በታማኝ ተቃዋሚነት ለማገልገል፡ ምርጫ ለፖለቲካ ሥልጣን ሳይሆን ለአጃቢ የፓርላማ ወንበር፡ ለአጨፋሪ ወንበር፡ ምርጫ ለግል ዝና ወዘተ. የታለመበትና የታቀደበት። ምርጫ ከወያኔ ዕይታ ካፈነገጠ መልሱ ጭፍጨፋ፡ እስርና ግድያ። ምርጫ በወያኔ ሕገ መንግሥት ሰጥ ለጥ ብሎ ለመገዛት ቃል መግባት። ምርጫ የወያኔን ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት መቀበል። ይህንና የመሳሰሉትን ነው ከግንቦት 97 ምርጫ የተማርነው። በተግባር የወያኔን ማንነትና ሂደት ይበልጥ ያረጋገጥንበት። ወያኔ መራጩን ሕዝብ ጨፍጭፎ ተመራጩን ለእስር የዳረገበት ትርይት ከሃዲና ባንዳ ዳግም የታየበት ትልቅ የትግል ትምህርት ዳግም የሚቀሰምበት ወቅት ግንቦት 97 ዛሬ የታሰሩት የቅንጅት መሪዎች በመፈታታቸው ትዝ ሊለን ይገዳል።

ወያኔ በ14 ዓመት አገዛዝ ዘመኑ በገጠሩ፡ በከተማው በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ያተረፈው ቢኖር ድጋፍን ሳይሆን ተቃውሞን፡ ተቀባይነትን ሳይሆን እምቢታን፡ ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻን፡ ሰጥ ለጥ ብሎ መገዛትን ሳይሆን እምቢታ በአደባባይ የታየበት ማዕበል ግንቦት 97 ብልጭታውን አሳይቶናል። በዚህ ትርይት ነው ሕዝቡ ተቃዋሚ ኃይሎችን በመምረጥ ቤቴን አስረክቡኝ፡ ቤተ መንግሥቱ ቤተ ሕዝብ ከሆነ ድምጼን ሰጥቻለሁና የነፃነት ቁልፌን፡ ሰላም ተብያለሁ - ሰላም ብያለሁ፡ ምርጫ ተብያለሁ - ምርጫ ብያለሁ፡ ይህ ነበር፡ ነውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻ ጥያቄ። ያላቋረጠ ተጋድሎና መስዋትነት እየተከፈለበት ያለ ትግል።

“የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንዲሉ ገና ወያኔ በትረ መንግሥቱን ከመጨበጡ፡ ሀገር በታኝ፡ ከፋፋይ አገዛዝ መሆኑን፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ የተቃጣ፡ የተወረወረ የማጥፋት ጥቃት፡ በወያኔ አስፈጻሚነት ሊተገበር ታሪካችንንና ሀገራችንን ለጥፋት ለመዳረግ ዓላማውና ግቡ አድርጎ የተነሳ አገዛዝ መሆኑን ሥልጣን ሳይዝም የጫካ ተግባሩን የሚያውቁ ከፍ አድርገው ድምፃቸውን አሰምተዋል። የሀገር ያለህ! የሕዝብ ያለህ! ብለዋል። የዚህ እኩይ ተግባሩ ትንሿ የሙከራ ክፍል ነው በግንቦት 97 የታየው። አሁንም ጆሮ ያለው ይስማ፤ ዓይን ያለው ይይ፤ ወያኔ ሀገርና ሕዝብ የማጥፋት ዕቅዱ ገና አልተነካም። ገና ብዙ እጅግ ብዙ የተግባር አጀንዳዎች አሉት። ወያኔ በምርጫ ፖለቲካ፡ በሰላም ሥልጣኑን በተለይ የኢትዮጵያን አንድነት ለሚፈልጉ ኃይሎች እንደማይለቅ ያሳየበትና የመሰከረበት ሕዝብ የመረጣቸውን ሲያስር፡ ሲጨፈጭፍ ሲገድል ካልተገነዘብንና ካልተረዳን “ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው”ን ልንተርክ ግድ ይለናል።

በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና በሕዝብ አንድነት ለምትገነባ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመሥረት ለሚሟገቱና ለሚታገሉ ኃይሎች የፖለቲካ ሥልጣን ማግኘት የማይመኙ ባዕዳን ኃይሎች በአለ አቅማቸው ድጋፋቸውን እስከተመቻቸው ድረስ ለወያኔ ይለግሳሉ። ደክሞም ከታያቸው ለሌላ አዲስ ጉልበት ላለው በታኝ ኃይል እገዛ ከማድረግ ወደ ኋላ እንዳላሉና እንደማይሉ እያየን ነው። ባዕዳን ኃይሎች ለጥቅማቸው ሲሉ ወያኔን ግፋበት፡ አይዞህ፡ በርታ ባዮች ከአፍሪካዊቷ ግብፅ ፡ ከአረቡ ዓለም ጀምሮ በለጸግን አሉት አሜሪካና እንግሊዝ፡ ሀገራችንን የሽቀጥ ማራገፊያ ያደረገችውና የሀገራችንን የተፈጥሮ ሀብት ለመዛቅ እያለመች ያለችው ቻይና ሁሉ ሀገርን እየሸጠ፡ ወጣቶችን ለዘመናዊ ባርነት እያስደደ፡ እየላከ፡ እየሸጠ ያለው ወያኔ ከሁሉም በላይ ተመችቷቸዋልና አሁንም ይመችህ ብለው ከመመረቅ፡ አነሰህ ብለው ከመለገስ፡ ግደልበት ብለው ጥይት ከማቀበል፡ አንድደው ብለው ክብሪት ከመጫር አይመለሱም። የወያኔ አገዛዝ በሂደት ቢያበቃለት እንኳ ቀጣዩ አራተኛ መንግሥት ሌላ ብሔር ይዞ፡ ሌላ ባንዲራ ተሸክሞ በአዲስ ኃይል፡ ሌላ በታኝ፡ ሌላ ከፋፋይ፡ በአዲስ መልክ የኢትዮጵያን መጥፋት ለሚመኝ ኃይል እያዘጋጁን መሆኑን ነጋሪና አስረጅ የሚያስፈልገው አለመሆኑን የትብብር ለአንድነትና ዲሞክራሲ (የAFD) ምሥረታና ዕቅድ በቂ ምስክር ነው።

የቅንጅት መሪዎችና አባላት መፈታት ወያኔ በፈቃዱ የሰጠው ገጸ በረከት ሳይሆን የትግል ውጤት ነው። ይህ ደግሞ እየተካሄደ ላለው ትግል የራሱ ድርሻና አስተዋጽዎ ይኖረዋል። በመሆኑም የቅንጅት መሪዎች ሊያነሷቸው የሚገባ ጥያቄዎች ይኖራሉ። መሠረታዊ የተነሳንበትን ዓላማ ሳንዘነጋ፡ እየታገልን ያለነው ለምንድነው? ጠላታችን ማነው? ያነገብናቸው ጥያቄዎች ምላሽ አግኝተዋል ወይ? የተነሳንበት ዓላማ ግቡን መቷል ወይ? የመሳሰሉት ጥያቄዎች እየታዩና ግንዛቤ እያገኙ መጓዝ ለፖለቲካ ድርጅቶች ቀጣይ ሂደታቸው ወሳኝነት ይኖረዋል።

ከግንቦት 97 ወዲህ የትግሉ መሪ መፈክር “የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!” መሆኑ ውቅታዊነቱን ጨምሮ የራሱ የሆነ መልዕክት አለው።

ወያኔ በሀገራችን ኢትዮጵያና በሕዝባችን ላይ የአገዛዝ መረቡን ከዘረጋ ጅምሮ የገደላቸው፡ ያሰራቸው፡ ደብዛቸውን ያጠፋቸው የሕዝብና የሀገር ልጆች በርካታ ናቸው። ይቀናቀኑኛል፡ ይቃወሙኛል ያላቸውን ወያኔ ማሰር፡ ማሰቃየት፡ ማሳደድ፡ መግደል የጀመረው በቅንጅት መሪዎችና አባላት ከግንቦት 97 ወዲህ አይደለም። ከአለፉት 16 ዓመታት ጅምሮ በወያኔ ማጐሪያ ቤት በየጊዜው እየማቀቁ ያሉት የፖለቲካ እስረኞች በርካታ ናቸው። አሁንም እየማቀቁ ይገኛሉ። ሁሉም የሕዝብ ወገኖች ናቸው። ሁሉም ወያኔን ሲፋለሙ፡ ሁሉም ለሀገራችን ሉዓላዊነትና ለሕዝብ

አንድነት ሲታገሉ፣ ሲያታግሉ ከወያኔ መዳፍ የወደቁ ናቸውና ስለ መፈታታቸው አበክረን ልንታገል፣ ልንጮህ ይገባናል። ለዚህም ነው “የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ” የሚለው መፈክር አሁንም ወቅታዊነት ያለው። ለአብነት አበራ የማነአብን፣ ፀጋዬ ገ/መድንን (ደብተራው)፣ አበራሽ በርታን አስሮና የት እንዳደረሳቸው ሳይታወቅ የትግሉ መፈክር ዝቅ አይልም። ተቃወሙኝ ያላቸውን በሺዎች የሚቆጠሩትን አፍኖ መፈክሩም ዝቅ አይል ትግሉም ጋብ አይልም። በሌላም መልኩ ወያኔ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሁሉንም የፖለቲካ እስረኞች ቢለቅ እንኳ የትግላችን ውጤት አርገን ለዘላቂው ግባችን ከመታገል ልንዘናጋ፣ ልንሞኝ፣ ልንታለል እንደማንችል ሊታወቅ ይገባል። የወጣቷን የሽብሬ ደሳለኝንና የበርካታዎችን ደም ያፈሰሱትን፣ ደም የጠጡትን ፍርዳቸውን ሳያገኙ፣ ተጠያቂነታቸውን ሳናስረግጥ ትግሉ ለአፍታም ጋብ አይልም። ትግላችን ለነፃነት፣ ገደብ ለሌለው የዲሞክራሲ መብት፣ ለሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥ ነውና !!!

“የሕዝብ ድምጽ ይከበር” ዛሬም ያላበቃለት፣ ሊጮህለት የሚገባ መፈክር። ከመርፌ ቀዳዳ በጠበበችው የግንቦት 97 ምርጫ ዲሞክራሲ ተጠቅሞ ማንነቱንና አይበገሬነቱን ያሳየው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ወያኔን ከአገዛዙ መንቅሎ ሊጥለው የተነሳውና የፈለገው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰጠው ድምጽ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነቱን አረጋግጧል። ይህ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መብት ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎበታል። ሕዝብ ቤቱን፣ ቤተ-መንግሥቱን ይፈልጋል። ሕዝብ ሀገሩን ይፈልጋል። ሕዝብ ድምጹን ይፈልጋል። ለዚህ ድምጽ መከበር ሌላ ድምጽ አይፈልግም። ለዚህ ድምጽ መከበር ለሌላ የሚዘረፍ ድምጽ ለመዘጋጀት ጆሮውም አይሰማም ትዕግስቱም የለውም። ትግልና መስዋዕትነት መክፈል በትንሹ ለ40 ዓመታት አብሮት ያለ ነውና ድምጹን አስከብሮ የሥልጣኑ ባለቤት ይሆን ዘንድ ለሀገሩ ባዳ አይደለምና በየቦታው እየታገለ ነው ያለው። በትግሉም ነፃነቱን፣ መብቱን እንደሚያረጋግጥ ነጋሪት መጐሰም አያስፈልገውም።

የቅንጅት መሪዎች በትግል መፈታት ራሱን የቻለ ድል ነው። ይህ ድል ደግሞ በቀጣይ ትግል ሊታገዝ ይገባዋል። ሕዝብ እንደመረጠ የሕዝብን ጥያቄ ከግቡ ለማድረስ በዓላማ ጸንቶ በቆራጥነት ከሕዝቡ ጋር መጓዝን ይጠይቃል። የቅንጅት መሪዎች በወያኔ እስር ቤት ከገቡበት ጊዜ አንስቶ በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረውን ውዥንብር፣ የፖለቲካ አካሄድ ከመመልከት አንስቶ ስለተደረገውና እየተደረገ ላለው ሂደት ብዙ ሥራና ምላሽ ይጠበቅባቸዋል። ከቃሊቲ ተፃፈ እየተባለ ከሚቀርበው ደብዳቤ፣ ሐተታ፣ መጽሐፍ ጀምሮ አሁን ቅንጅት አለበት ደረጃ ድረስ ያለውን ትርምስ እውን ያውቁታልን? እውን ተቀብለውታልን? ቀጣዩስ የትግል ሂደት ከቅንጅት አኳያ እንዴት ነው? ብዙ በርካታ ጥያቄዎች ተደቅነው ይጠብቋቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴምነቱ የጣለባቸውን ሀላፊነት ከጐኑ ቁመው፣ አብረውት ተሰልፈው፣ ከወያኔ ልጓም ተላቆ መብትና ነፃነቱን በትግሉ አግኝቶ፣ በአገሩና በህልውናው ወሳኝ ሚና የሚጫወትበትን ወቅት ይናፍቃልና ለዚህ ስኬታማነት በግለሰብም ሆነ በድርጅት ደረጃ የድሉን ፍሬ እስኪያገኝ ድረስ ሁሉም አብሮት እንደሚጓዝ እምነቱ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና፣ ስለ ሕዝቡ አንድነት የቅንጅት አቋም እንዴት ነው? AFDን እንዴት ያዩታል? ሁለቱ የቅንጅት አካላት ቅንጅት ዓለም አቀፍ (KIL) እና ቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል (KIC) የተወዛገቡበትን ጉዳይ ያውቁታልን? ቅንጅት ዓለም አቀፍ (KIL) እና ቅንጅት ዓለም አቀፍ ካውንስል (KIC) ከAFD ጋር ያላቸውን ትስስር እንዴት ያዩታል? ከእስር ከተፈቱት የቅንጅት አመራር አካላት ለአለፉት 18 ወራት የተፈጠረውን ውዝግብና የትግል አቅጣጫውን ፈር የማስለቀቅን ሂደት መገምገምና አካሄዱን መመርመርና ጥርት ያለ አቋም መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። በአጠቃላይ የቅንጅት ዓላማ የሕዝብ እስከሆነ ድረስ ሕዝብ ደግሞ ሀገሩንና ባንዲራውን ይወዳል፣ ይፈልጋልና የተፈጠረውን ውዝግብ አርግበውና ፈትተው ከኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ጋር በመተባበር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ከተደቀነባቸው አደጋ ለማዳን መነሳሳት

ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦችን፣ ምሁሮችን በማካተት ለሚደረገው የጋራ ትግል መሰባሰቢያ መድረክ እንቅፋት የሆነውን የAFDን ምሥረታ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር ይሆን ዘንድ፣ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር ከሌላው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር መፍትዬ ማግኘት የሚገባው መሆኑንና ሀገሪቷን ለዳግም መበታተን እየደለቱ ያሉ ኃይሎችን ለመታገል በጋራ የጋራ ትግል ፈር የሚይዝበትን መንገድ ለመቀየስ ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋጽዎ ቀላል አይደለምና ሕዝብ እንዳመነባቸው፣ የሕዝብን ድምጽ ሰምተው ለእስር እንደተዳረጉ ሁሉ የሕዝብ ጥያቄ በድል እስኪጠናቀቅ ድረስ ስለ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር መቆም የግድ ይላል።

ትግሉ ለወያኔ ሽርፍራፊ የፓርላማ ወንበር ከሆነ መታሰርም ባላስፈለገ። ትግሉ ለሁሉም የፖለቲካ እስረኞች መፈታት ካልሆነ መታሰርም ባላስፈለገ። ትግሉ ገደብ ለሌለው የዲሞክራሲ መብት፣ ለሕዝብ ድምጽ መከበር፣ ለሕዝብ መንግሥት መመስረት ካልሆነ መታሠር፣ መገደል ባላስፈለገ። ትግሉ በአገዛዙ ለተገደሉ ወገኖቻችን ሁሉ ደም አፍሳሾችን፣ ሕይወት ቀጣፊዎችን ለፍርድ ለማቅረብ፣ ተጠያቂነታቸውን በውድም ሆነ በግድ ማሳየት፣ ትግሉ የሀገሪቷን ሀብትና ንብረት ያለ አግባብ የዘረፉትንና እየዘረፉ ያሉትን አለአግባብ የበለጸጉትን ዘራፊውች ለተጠያቂነት ማቅረብ፣ ትግሉ አጠቃላይ ኢትዮጵያችን ሁሉም ሕዝብ በጋራና በነፃነት የሚኖርባት ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት ከሆነ የሕዝብን ፍላጎት ማሟላት ቀዳሚውን ቦታ ይይዛልና "የሕዝብ ድምጽ ይከበር" አሁንም ወቅታዊ መፈክር።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር ሲባል፣ ወያኔ ሥልጣኑን ያለ ምንም ሽርፍራፊና ቅድመ ሁኔታ ለሕዝብ ያስረክብ ማለት ነው።
የሕዝብ ድምጽ ይከበር ሲባል፣ «ላምባገነን መንግሥት ሕዝቡን ላልወከለ፣ አይገዛም፣ አይገዛም ሕዝቡ ሳለ እየታገለ» መዘመር ማለት ነው።

የሕዝብ ድምጽ ይከበር!!!
የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!